| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ድርሰት ። |
| ርእስ ፤ | "የከፋ ፡ ታሪክ ፡ እንዳይደገም ፥<br>ዐጪር ፡ ማሳሰቢያ ። " |
| ደራሲ ፤ | ምንደሲል ፡ ፀሓዩ |
| ዕለት ፤ | መስከረም ፡ 2012 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፥ ቍ.2012-001 ። |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | (የግል ፡ አስተያየት ። ) |

# ድርሰት

Essay | Essai | مَقال

# የከፋ ፡ ታሪክ ፡ እንዳይደገም ፥ ዐጪር ፡ ማሳሰቢያ ።

ምንደሲል ፡ ፀሓዩ

---

ዛሬ ፡ ባገራችን ፡ የምናየው ፡ ችግር ፡ ተጠንቶ ፡ የታቀደ ፡ የረዥም ፡ ጊዜ ፡ ሥራ ፡ ውጤት ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ይቻላል ። ለመቶ ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ የምዕራቡ ፡ ዓለም ፡ ኀያላን ፡ መንግሥታት ፥ *« ኢትዮጵያን ፡ አላስደፍር ፡ ብሎ ፡ ያቈያት ፡ ዐማራ ፡ የተሠኘው ፡ ክፊል ፡ ሕዝብ ፡ ነው »* ፡ ብለው ፡ ስላመኑ ፥ *« ኢትዮጵያን ፡ እንደሌላው ፡ ያፍሪቃ ፡ ሀገሮች ፡ የምናንበረክካት ፥ ይህን ፡ ዐማራ ፡ የተሠኘውን ፡ ሕዝብ ፡ ስናንበረክክ ፡ ብቻ ፡ ነው »* ፡ ብለው ፡ የማያከትም ፡ ዘመቻ ፡ ዠመሩ ። ዐላማቸውን ፡ ለመፈጸም ፡ ዐማራ ፡ ነው ፡ ያላሉትን ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ *« ዐማራ ፡ ጨቈኖኻል ፥ ካማራ ፡ ቀንበር ፡ ውጣ »* ፡ እያሉ ፡ በተለያየ ፡ መንገድ ፡ መስበክ ፡ ዠመሩ ።

ያሳዝናል ፥ የኢትዮጵያን ፡ ወጣቶች ፡ ለማስተማር ፡ የተመለመሉት ፡ የውጪ ፡ መምህሮች ፡ ኢትዮጵያ ፡ ቀኍጭ ፡ ብለው ፡ በዚሁ ፡ ስብከት ፡ የወጣቱን ፡ ገር ፡ አእምሮ ፡ ሲበክሉ ፡ አንድ ፡ ያላቸው ፡ የለም ። ትንሽ ፡ ዓመታት ፡ በ፟ኋላ ፡ እነዚሁ ፡ ወጣቶች ፡ ባግባብ ፡ ኾነ ፡ አላግባብ ፡ ሥልጣን ፡ ሲይዙ ፥ እንደታቀደው ፥ የጠላትን ፡ ዕቅድ ፡ እዳር ፡ ለማድረስ ፡ በትጋት ፡ ሠሩ ፤ አገርን ፡ ማፈራረስ ፡ ዠመሩ ።

ዋናው ፡ ዘዴ ፤ *"የብሔር ፡ እኩልነት"* ፡ የሚሉት ፡ ዘይቤ ፡ ነው (በስሕተት ፡ *"ብሔር"* ፡ ብለው ፡ የሚሰይሙት ፡ ጎሳን ፡ ወይም ፡ ነገድን ፡ ነው) ። እኩልነት ፡ በመብት ፡ እንጂ ፡ በሌላ ፡ አይደለም ። ለዚህም ፡ እኩል ፡ የሚባለው ፡ በሕግ ፡ ህልውና ፡ ያለው ፡ ዜጋ ([1]) ፡ እንጂ ፡ በሕግ ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ ዕውቅና ፡ የሌለው ፡ ነገድ ፡ ወይም ፡ ጎሳ ፡ አይደለም ። እኩሉ ፡ ሰውና ፡ ሰው ፡ እንጂ ፡ ነገድና ፡ ነገድ ፡ አይደለም ። ሰውና ፡ ሰው ፡ እኩል ፡ ከኾነ ፡ ከቶ ፡ የ*"ብሔር"* ፡ እኩልነት ፡ ለምን ፡ ይጠቅማል?

የሚጠቅመው ፥ ሕዝብን ፡ በዘር ፡ ለያይቶ ፡ አገርን ፡ ለማድከም ፡ ነው ። ለምሳሌ ፥ በቋንቋ ፡ ረገድ ፥ የትውልድ ፡ ቋንቋው ፡ ዐማርኛ ፡ ያልኾነ ፡ ኹሉ ፤ *« የነገዴ ፡ ቋንቋ ፡ ካማርኛ ፡ አያንስም ፤ መተዳደሪያዬ ፡ ይኹንልኝ »* ፡ ሲል ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ አንድ ፡ የሚያደርገውን ፡ ልሳን ፥ ዐማርኛን ፡ ዐጥቶ ፡ ወዳለመግባባት ፡ ወደ ፡ መለያየት ፡ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ እንዲያመራ ፡ ይኾናል ።

ሌላው ፡ ዘይቤ ፡ ደግሞ ፡ *"የሃይማኖት ፡ እኩልነት"* ፡ ነው ። እኩልነቱ ፡ የፈቀዱትን ፡ ሃይማኖት ፡ የመከተል ፡ መብት ፡ እንጂ ፡ የሃይማኖት ፡ [እኩልነት] ፡ አይደለም ። ከቶ ፡ *"ሃይማኖቴ ፡ ከሌላው ፡ ይበልጣል"* ፡ እንጂ ፡ *"እኩል ፡ ነው"* ፡ የሚል ፡ የለም ። ዐላማው ፥ ታሪክ ፡ እንደሚያሳየው ፥ የኢትዮጵያን ፡ አንድነት ፡ ይዛ ፡ ለማቈየት ፡ (በተለይ ፡ ዐማርኛን ፡ ዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ በማስፋፋት) ፡ ከምንም ፡ ከማንም ፡ በላይ ፡ የሠራችውን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ደረጃ ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ያገር ፡ አንድነትን ፡ የመሸርሸርን ፡ ሥራ ፡ አለዕንቅፋት ፡ ማካኼድ ፡ ነው ።

የሚያሳዝነው ፥ ዛሬ ፥ *« ዐማራ ፡ ተጠቃ »* ፡ ብሎ ፥ የኢትዮጵያን ፡ አንድነት ፡ ቈርቋሪውን ፡ *« እንደ ፡ ጎሳ ፥ ስም ፡ ለይተኽ ፡ ተደራጅ »* ፡ (በሌላ ፡ አነጋገር ፡ የኢትዮጵያን ፡

---

1 *"ዜጋ"* ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ *"ተገዥ"* ፡ ማለት ፡ ነው ፤ በፈረንጅና ፡ "subject" ፡ ለሚለው ፡ ይስማማል ። የሀገር ፡ ባለቤት ፣ ሀገሬ ፣ ሀገረኛ ፥ ወይም ፡ በፈረንጅኛ ፡ "citizen" ፡ ለማለት ፡ *"ሀገራዊ"* ፡ የሚለው ፡ ቃል ፥ በቅጽልነቱ ፡ ሳይኾን ፥ በስምነቱ ፡ የተሻለ ፡ ጕዳዩን ፡ ይገልጸዋልና ፥ ቃሉን ፡ በ*"ሀገራዊ"* ፡ ወይም ፡ በ*"ሀገረኛ"* ፡ ተክቶ ፡ ማንበብ ፡ ይቻላል ። [አዘጋጅ]


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2012 ፡ ዓ.ም. ።

መገነጣጠል ፡ እዳር ፡ አድርስ) ፡ እያለ ፡ የሚሰብከው ፡ አካል ፡ በመሠረቱ ፥ እላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ እኩይ ፡ ዕቅድ ፡ ፈጻሚ ፡ መኾኑ ፡ ላስተዋለ ፡ ሰው ፡ ግልጽ ፡ ቢኾንም ፥ የተከታዩ ፡ ወጣት ፡ ገር ፡ አእምሮ ፡ ይህን ፡ እውነት ፡ አልተገነዘበውም ። ዳግመኛ ፡ እንደዛሬ ፡ ስድሳ ፡ ዓመት ፥ አገርን ፡ ለማፍረስ ፡ ሲሰበክ ፥ ቁም ፡ ነገሩ ፡ አልገባውም ።

የከፋ ፡ ታሪክ ፡ እንዳይደገም ፡ የበሰለው ፡ ትውልድ ፡ እውኑን ፡ ሊያስገነዝበውና ፡ ማስተዋል ፡ የከለከለውን ፡ የወጣት ፡ ወኔውን ፡ *« ዛሬም ፡ ነገም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ነኝ »* ፡ ብሎ ፥ ላገር ፡ አንድነት ፡ እንዲያውል ፡ አለመታከት ፡ ሊመክረውና ፡ መልካም ፡ አግጣጫን ፡ አስይዞ ፡ ወደ ፡ መልካም ፡ ፍጻሜ ፡ ሊመራው ፡ ከባድ ፡ ኀላፊነት ፡ አለበት ❖


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2012 ፡ ዓ.ም. ።